የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETA

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ዘጠነኛ ዓመት ቁጥር ፲
አዲስ አበባ—ኅዳር ፭ ቀን ፲፱፻፺፭

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

9th Year No. 10
ADDIS ABABA–14th November, 2002

## ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፪፻፺፰/፲፱፻፺፭ ዓ.ም

ለገጠር የፋይናንስ ሥርዓት ማስፋፊያ ፕሮግራም ማስፈጸሚያ ከዓለም አቀፍ የግብርና ልማት ፈንድ ብድር ለማግኘት የተፈ ረመው የብድር ስምምነት ማጽደቂያ አዋጅ ..... ገጽ ፩ሺ፱፻፵፱

## CONTENTS

Proclamation No. 298/2002

International Fund for Agricultural Development Loan Agreement for Financing Rural Financial Intermediation Programme Ratification Proclamation ........................................................... Page 1949

## አዋጅ ቁጥር ፪፻፺፰/፲፱፻፺፭

## በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በዓለም አቀፍ የግብርና ልማት ፈንድ መካከል የተደረገውን የብድር ስምምነት ለማጽደቅ የወጣ አዋጅ

ለገጠር የፋይናንስ ሥርዓት ማስፋፊያ ፕሮግራም ማስፈጸሚያ የሚውል መጠኑ ኤስ.ዲ.አር. ፳ ሚሊዮን ፩፻፶ ሺህ (ሃያ ሚሊዮን አንድ መቶ ሃምሳ ሺህ ኤስ.ዲ.አር) የሆነ ገንዘብ የሚያስገኘው የብድር ስምምነት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በዓለም አቀፍ የግብርና ልማት ፈንድ መካከል እ.ኤ.አ. ጃንዋሪ ፲፬ ቀን ፪ሺ፪ በሮም የተፈረመ በመሆኑ፣

መሠረታዊ የኢኮኖሚ ዓለም አቀፍ ውሎች ተፈጻሚ ከመሆናቸው በፊት መጽደቅ ስላለባቸው፣

ይህንኑ የብድር ስምምነት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ኅዳር ፭ ቀን ፲፱፻፺፭ ዓ.ም ባደረገው ስብሰባ ያጸደቀው ስለሆነ፣

በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ ፶፭ ንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፲፪) መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

፩. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "ለገጠር የፋይናንስ ሥርዓት ማስፋፊያ ፕሮግራም ማስፈጸሚያ ከዓለም አቀፍ የግብርና ልማት ፈንድ ብድር ለማግኘት የተፈረመው የብድር ስምምነት ማጽደቂያ አዋጅ ቁጥር ፪፻፺፰/፲፱፻፺፭" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

## PROCLAMATION NO. 298/2002

## A PROCLAMATION TO RATIFY THE LOAN AGREEENT BETWEEN THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA AND THE INTERNATIONAL FUND FOR AGRICULTURAL DEVELOPMENT

WHEREAS, a Loan Agreement, between the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the International Fund for Agricultural Development stipulating that the International Fund for Agricultural Development provide to the Federal Democratic Republic of Ethiopia a Loan amount of SDR. 20,150,000 (twenty million one hundred and fifty thousand Special Drawing Rights) for financing rural Financial Intermediation Programme, was signed in Rome, on the 14th day of January, 2002;

WHEREAS, basic economic international agreements have to be ratified prior to entry into force;

WHEREAS, the House of Peoples' Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified said Loan Agreement at its session held on the 14th day of November, 2002;

NOW, THEREFORE, in accordance with Article 55 Sub-Articles (1) and (12) of the Constitution, it is hereby proclaimed as follows:

1. *Short Title*

This Proclamation may be cited as the "International Fund for Agricultural Development Loan Agreement for Financing Rural Financial Intermediation Programme Ratification Proclamation No. 298/2002"

ያንዱ ዋጋ
Unit Price 2.30

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ. ፹ሺ፩
Negarit G.P.O.Box 80,001

፪. <u>ትርጓሜ</u>
በዚህ አዋጅ ውስጥ "የብድር ስምምነት" ማለት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በዓለም አቀፍ የግብርና ልማት ፈንድ መካከል እ.ኤ.አ. ጃንዋሪ ፲፬ ቀን ፪ሺ፪ በሮም የተፈረመው ቁጥር ፭፻፸፪–ኢ.ቲ. የብድር ስምምነት ነው።

፫. <u>የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስትሩ ሥልጣን</u>
የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስትሩ በብድር ስምምነቱ የተገኘውን ኤስ.ዲ.አር. ፳ ሚሊዮን ፩፻፶ ሺህ (ሃያ ሚሊዮን አንድ መቶ ሃምሳ ሺህ ኤስ.ዲ.አር.) በብድር ስምምነቱ በተመለከቱት ሁኔታዎች መሠረት በሥራ ላይ እንዲውል ለማድረግ በዚህ አዋጅ ሥልጣን ተሰጥቶታል።

፬. <u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>
ይህ አዋጅ ከኅዳር ፭ ቀን ፲፱፻፺፭ ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል።

አዲስ አበባ ኅዳር ፭ ቀን ፲፱፻፺፭ ዓ.ም

ግርማ ወልደጊዮርጊስ
የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ፕሬዚዳንት

2. *Definition*
In this Proclamation "Loan Agreement" means the Loan Agreement Number 572 – ET signed in Rome, on the 14th day of January, 2002, between the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the International Fund for Agricultural Development.

3. *Power of the Minister of Finance and Economic Development*
The Minister of Finance and Economic Development is hereby empowered to undertake all acts necessary for the utilization of the Loan amount of SDR. 20,150,000 (twenty million one hundred and fifty thousand Special Drawing Rights) in accordance with the terms and conditions set forth in the loan agreement.

4. *Effective Date*
This proclamation shall enter into force as of the 14th day of November, 2002.

Done at Addis Ababa, this 14th day of November, 2002.

GIRMA WOLDE GIORGIS
PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC
REPUBLIC OF ETHIOPIA

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ታተመ
BREHENENA SELAM PRINGING ENTERPRISE